## የህዝቦች ትብብር ለነጻነትና ለዴሞክራሲ ወቅታዊ መግለጫ

## (ኦነግ ኦብነግ ሲነግ እና ሌሎች የትብብሩ እጩ ኣባል ድርጅቶች)

ከላይ ስማቸው የተጠቀሰው የኦጋዴን፣ የኦሮሞ፣ የሲዳማ እና የሌሎችም የትብብሩ እጩ ኣባላት:

የወቅቱን የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታ እንዲሁም በስልጣን ላይ ባለው ስርኣት ላይ የሚደረገው ህዝባዊ ትግል የሚገኝበትን ደረጃና ላለፉት ሃያ አንድ ኣመታት ሃገሪቱን ሲገዛ የኖረው መለስ ዜናዊ በድንገት ደብዛው መጥፋቱን ተከትሎ የተከሰተውን ግራ መጋባት በመገንዘብ፣

በስልጣን ላይ ያለው መንግስት መለስ ዜናዊን የገጠመውን እጣ በምስጢር እንደ ያዘ የኢትዮጵያ ህዝቦችን እያታለለ ኣሁን ያለውን የጭካኔ ኣገዛዝ እንዳለ ለመቀጠል ማቀዱ ኣሳሳቢ በመሆኑ፣

ኣንዳንድ የፖለቲካ ተቃዋሚ ቡድኖች ባለፉት ኣርባ ኣመታት ትግል በኢትዮጵያ የታዩትን የማህበራዊና የፖለቲካ ለውጦችን ኣምነው ባለመቀበልና ባለማክበር በ21ኛው ክፍለ ዘመን ጨርሶ ተቀባይነት ከሌለው ያረጀ ያፈጀ የፖለቲካ ኣስተሳሰብ መላቀቅ ተስኖኣቸው የብሄሮችና የብሄረሰቦችን የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት መቃወማቸውን በመገምገም፣

ኣንዳንድ የፖለቲካ ተቃዋሚ ወገኖች ባገኟቸው ኣጋጣሚዎች ሁሉ በወደፊቱ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ለውጥ ማግስት ስላላቸው ምኞት በሚያሰሟቸው ንግግሮች ተጨቁዋኝ ህዝቦች ኣሁን ብቻ ሳይሆን ዛሬ በስልጣን ካለው ስርኣት በፊት በነበሩት የመንግስት ስርኣቶች ውስጥም ተገቢ ቦታ ሲነፈጉ፣ በደል ሲፈጸምባቸው፣ በባርነት ደረጃ መታየታቸውንና ከዚህ የፖለቲካ ኣፈና ለመላቀቅ ለዘመናት ያካሄዱትን ትግል እነዚህ ሃይሎች እንደማይቀበሉ በመረጋገጡ፣

ኣንዳንድ የተቃዋሚው ፖለቲካ ጎራ ኣካላት ስልጣን ላይ ያለው መንግስት ሳይቀር በመርህ ደረጃም ቢሆን ተቀብሎት ገቢራዊ ለማድረግ ግን ያልፈቀደውን የብሄር ብሄረሰቦችን የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ከነኣካቴው ለመቀልበስ ጥልቅ ፍላጎት እንዳላቸው ግልፅ በመሆኑ፣

ቀደም ካለው ወቅት ኣንስቶ ደማቸውን በመገበር ለመብታቸው ሲታገሉ የቆዩትና ዛሬም በስልጣን በሚፈራረቁት የኢትዮጵያ ገዢዎች ላይ መራራ ፍልሚያ እያካሄዱ ያሉት ብሄር ብሄረሰቦች እስካሁን በትግላቸው የጨበጧቸው ድሎች እንዲቀለበሱ ከቶውንም እንደማይፈቅዱ በማስገንዘብ የህዝቦች ትብብር ለነጻነትና ለዴሞክራሲ እንደገና የሚከተሉትን ነጥቦች በኣጽንኦት ማስገንዘብ ይወዳል።

1. ሰላማዊና ስርኣት ባለው መልኩ የፖለቲካ ስልጣንን ለኢትዮጵያ ህዝቦች ማስረከብ የሚቻለው የብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ተወካዮች እንዲሁም፣ ለትክክለኛው ዴሞክራሲ መስፈን በቅንነት ታግለው የኢትዮጵያን ኢምፓየራዊ ገጽታ ለመቀየር የተዘጋጁ ወገኖችን ያሳተፈ ኣጠቃላይ ኮንፈረንስ ሲካሄድ ብቻ ይሆናል።

2. የወደፊቱን የኢትዮጵያ ፖለቲካ በአዲስ መልክ ማዋቀር የሚቻለው የራስን እድል በራስ የመወሰን፣ የግልና የቡድን መብቶችን ጨምሮ ለእውነተኛው የዴሞክራሲ መርሆዎች በመገዛት ብቻ ይሆናል።
3. ለዘመናት ስር የሰደዱ የፖለቲካ አለመግባባቶችን ማስወገድ የሚችሉ የፖለቲካ ለውጦችና የፖለቲካ ስርአት አወቃቀሮች በኢትዮጵያ ገቢራዊ መሆን የሚችሉት በሃገሪቷ ባሉ ብሄሮችና ብሄረሰቦች እውነተኛ ፍላጎትና እምነት ላይ ሲመሰረቱ ብቻ ነው።
4. በስልጣን ላይ ያለውን ስርአት ጨምሮ ማንኛውም የፖለቲካ ቡድን የኢትዮጵያን ብሄሮችና ብሄረሰቦችን የወደፊት እጣ በእነ-አውቅልሃለሁ ፈሊጥ ሊወስንላቸው አይችልም።
5. የህዝቦች ትብብር ለነፃነትና ለዴሞክራሲ እስከ ዛሬ በኢትዮጵያ ግፈኛ ስርአቶች ስር ለመከራ ህይወት የተዳረጉትን ብሄሮችና ብሄረሰቦች ሁሉ አንድ ላይ በማደራጀት ለነጻነትና ለዴሞክራሲ የሚደረገውን የተቀናጀ ትግል እንዲያካሄዱ ለማስቻል የሚያበረክተውን ሚና በይበልጥ ያሳድጋል።
6. አለም አቀፉ ማህበረሰብ የኢትዮጵያ ብሄሮችና ብሄረሰቦች ሁሉ ያላቸውን ፍላጎቶች፣ ምኞቶችና መብቶች በማክበርና በመደገፍ አሁን ያለው የፖለቲካ ሁኔታ ባለበት መቀጠል እንደማይችል እንዲያውም ሌላ ተጨማሪ አደጋ የሚጋብዝ መሆኑን እንዲረዱ እናሳስባለን።

በመጨረሻም የህዝቦች ትብብር ለነፃነትና ለዴሞክራሲ ስልጣን ላይ ያለውን መንግስትም ጨምሮ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ፓርቲዎች ሁሉ እንዲሁም የብሄሮችና ብሄረሰቦች ተወካዮችን በሙሉ የሚያሳትፍ፣ ኢትዮጵያን ለገጠመው የፖለቲካ ግራ መጋባት መፍትሄ የሚያፈላልግ አጠቃላይ ኮንፈረንስ በዚህ ታሪካዊ አጋጣሚ በአለም አቀፉ ማህበረሰብ አስተባባሪነት እንዲዘጋጅ ጥሪ ያቀርባል።

ኦብነግ

ኦነግ

ሲነግ

አዳዲስ የትብብሩ እጩ አባል ድርጅቶች

Contact: thepeoplesafd@gmail.com